# ግሎባል ጋግ ሩል በኢትዮጵያ
# የተዋልዶ ጤና ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

GUTTMACHER INSTITUTE

**የግሎባል ጋግሩል ተግባራዊ በተደረገባቸው ዓመታት የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎቶችና ተያያዥ ጉዳዮች የተጎዱ ሲሆን የፅንስ ማቋረጥ አገልግሎት ግን መሻሻልን አሳይቷል**

| መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች | የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት | የተዋልዶ ጤና ጉዳዮች | የፅንስ ማቋረጥ አገልግሎት |
| --- | --- | --- | --- |
| -እንቅስቃሴ ተስተጓጉሏል፣ አጋርነት ተስተጓጉሏል፣<br>-ፕሮግራሞች ታጥፈዋል ወይም ተቋርጠዋል | -በመንግስት ጤና ተቋም አማካኝነት የሚሰጡ የደርሶ መልስ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ቀንሷል።<br>-የእርግዝና መከላከያ አቅርቦትና አገልግሎት ቀንሷል። | የዘመናዊ የእርግዝና መከላከያ አጠቃቀም የቀነሰ ሲሆን የውልደት መጠን ጨምሯል | -በመንግስት ጤና ተቋማት የሚሰጠው የፅንስ ማቋረጥ<br>አገልግሎት ጨምሯል።<br>-ጥንቃቄ የተሞላበት የፅንስ ማቋረጥ<br>አገልግሎት ጨምሯል<br>-የድህረ ውርጃ ህክምና ቀንሷል |

የትራምፕ አስተዳደር ግሎባል ጋግ ሩል (Global Gag Rule) አሁን እየተተገበረ ባይሆንም በኢትዮጵያ የተዋልዶ ጤና ዘርፍ ላይ ዘላቂ የሆነ ተፅዕኖ ሊያስከትል ይችላል። ግሎባል ጋግ ሩል ተብሎ የሚጠራው የገንዘብ ድጋፍ ማዕቀብ እ.ኤ.አ. ከግንቦት 2007 እስከ 2021 በፅንስ ማቋረጥ ዙሪያ መረጃና የምክር አገልግሎት የሚሰጡ፣ የፅንስ ማቋረጥ አገልግሎትና ሪፈራል እንዲሁም የአድቫከሲ ስራ የሚሰሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከአሜሪካ መንግስት የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት እንዳይችሉ አድርጓል። ይህ ፖሊሲ ለመጀመሪያ ጊዜ ተግባር ላይ የዋለው እ.ኤ.አ በ1984 ሲሆን ሪፐብሊካን ፕሬዝዳንቶች በሚመረጡበት ወቅት በተግባር ላይ የሚውል ሲሆን በዲሞክራት ተመራጭ ፕሬዚደንቶች ወቅት ይህን ፖሊሲ ተግባር ላይ እንዳይውል ያደርጉታል፡ ፡ ዲሞክራቶች እንዳይተገበር ያቆሙትን እ.ኤ.አ ፖሊሲ የትራምፕ አስተዳደር በ2017 እንደገና ወደነበረበት እንዲመለስ ያደረገው ሲሆን ይዘቱንም በማስፋፋት እገዳው በሁሉም የአሜሪካ የአለም ዓቀፍ ድጋፍ ሰጪ ተቋማት በኩል እንዲተገበር አድርጓል። እ.ኤ.አ በግንቦት 2019 ደግሞ ፖሊሲውን ይበልጥ በማጠናከር እገዳው በትብብር የሚሰሩ ሶስተኛ ወገን (sub grantees) መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ላይ እንዲተገበር ሆኗል። እ.ኤ.አ በታህሳስ 2021 አዲሱ የባይደን አስተዳደር ፖሊሲው በተግባር ላይ እንዳይውል አድርጓል።

ይህ መረጃ የቤተሰብ እቅድ ከሚሰጡ 361 የጤና ተቋማት እንዲሁም እድሜያቸው በመውለድ እድሜ ክልል ውስጥ ባሉ 4,909 ሴት ተጠያቂዎችን በማሳተፍ የተደረገ የጥናት ውጤት የያዘ ነው፡ ፡ ትንታኔው ፖሊሲው ከመተግበሩ በፊትና ሙሉ በሙሉ ከተፈፀመ በኋላ (2017 እና 2020) መካከል ያለውን እንቅስቃሴና ያስከተለውን ውጤት በንፅፅር የሚያሳይ ነው። የጥናቱ ውጤት የአገሪቱ 90% የሚሆነው ህዝብ ከሚኖርባቸው ክልሎች ማለትም አዲስ አበባ፣ አፋር፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ትግራይና የደቡብ ህዝቦችና ክልሎች ከተገኘ መረጃን መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው።

## መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ላይ ያስከተለው ተፅዕኖ

- በርካታ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከአሜሪካ መንግሥት የሚያገኙትን የገንዘብ ድጋፍ ላለማጣት ሲሉ ትራምፕ ያሻሻለውን የጋግ ሩል በመቀበል ስምምነታቸውን ገልፀዋል። በመሆኑም የነበራቸው የአጋርነት ሥራ የተስተጓጎለ ከመሆኑም በላይ ያቀርቡት የነበረው የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ይዘት ቀንሷል ወይም ተቋርጧል።
- ጥቂት መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የፅንስ ማቋረጥ አገልግሎትን አቁሙ የሚለውን ፖሊሲ ባለመቀበላቸው ከአሜሪካ መንግስት የሚያገኙት የገንዘብ ድጋፍ ተቋርጦባቸዋል፡ ፡ በመሆኑም እ.ኤ.አ በ2019 ሁለት ትላልቅ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚሰጧቸው አገልግሎቶች ተስተጓጉሏል። ይህም
  - > በ24 ወረዳዎች ይሰጡ የነበሩ የወጣቶች የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ቀንሶ በ18 ወረዳዎች ብቻ እንዲሆን ተደርጓል
  - > የረጅም ጊዜና የቋሚ የእርግዝና መከላከያ አገልግሎት የሚሰጥባቸው የተንቀሳቃሽ አገልግሎት መስጫ ፕሮግራም ታጥፏል
  - > ለመንግስት የጤና ተቋማት የቴክኒክ ድጋፍ የሚያደርጉ ፕሮግራሞች ተቋርጠዋል።

## በቤተሰብ እቅድ አገልግሎቶች ላይ ያስከተለው ተፅዕኖ

የጋግ ሩል ፖሊሲ በተግባር ላይ በዋለበት ጊዜ ዉስጥ (ከ2017 እስከ  2020) የተለያዩ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት አቅርቦት  ቅነሳ አሳይቷል። እ.ኤ.አ በ2020 ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አገልግሎት የሚሰጡ የጤና ተቋማትና አገልግሎት ብዛት ከ2017 ጋር ሲነፃፀር ቅነሳ አሳይቷል።

- በማህበረሰብ በጎ ፈቃደኞች የሚሰጠዉ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ከ30% ወደ 24% ዝቅ ብሏል
- የደርሶ መልስ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት አሰጣጥ ከ21% ወደ 8% ዝቅ ብሏል
- የተቀናጀ የቤተሰብ እቅድና የድህረ ፅንስ ማቋረጥ አገልግሎት ከ77% ወደ 73% ዝቅ ብሏል
- የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች እጥረት ያጋጠማቸው የጤና ተቋማት ከ53% ወደ 59% ከፍ ብሏል

## በተዋልዶ ጤና ላይ ያስከተለው ተፅዕኖ

- ፖሊሲው ተግባራዊ ከሆነ በኋላ በቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ላይ የታየው ቅነሳ በኢትዮጵያ ውስጥ አገልግሎቱን በማስፋፋት ረገድ የተገኘውን አጥጋቢ እመርታ እንዲቀለበስ ያደረገ ከመሆኑም በላይ በእርግዝና መከላከያ አጠቃቀም ላይና በተዋልዶ ጤና ጉዳዮች ዙሪያ አሉታዊ ተፅዕኖ አስከትሏል። እ.ኤ.አ. በ2018 እና በ2020 መካከል የሚከተሉት ለውጦች ታይተዋል።
- በቅርብ አመታት እየታየ ያለው ዘመናዊ የእርግዝና መከላከያ የሚጠቀሙ ሴቶች ምጥነት ፖሊሲው ተግባራዊ ከሆነ በኋላ አካሄዱ እየተቀለበሰ (እየቀነሰ) መጥቷል።

- ይህ ለውጥ በገንዘብ እቀባ ምክንያት አገልግሎት ካልተቋረጠባቸው አካባቢዎች ጋር ሲነፃፀር በገንዘብ መቋረጥ ምክንያት አገልግሎት በተቋረጠባቸው አካባቢ ከፍ ያለ ነው።

- በአገሪቱ ውስጥ የውልደት መጠን እየቀነሰ ያለ ቢሆንም ጥናቱ በተካሄደባቸው ስፍራ ያሉ ልጅ የወለዱ ሴቶች ብዛት ከ14 ወደ 16 በመቶ ከፍ ብሏል።

## በየፅንስ ማቋረጥ አገልግሎቶች ላይ ያስከተለው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ. በ2005 ኢትዮጵያ የፅንስ ማቋረጥ ሕግን በማሻሻል ሴቶች ሰፋ ባለ ሕጋዊ አግባብ አገልግሎቱን እንዲያገኙ አድርጋለች። ይህንንም ተከትሎ ጥንቃቄ የተሞላበት የፅንስ ማቋረጥ እንዲሁም የድህረ ውርጃ አገልግሎትን በማዳረስ ረገድ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። የኢትዮጵያ የጤና ዘርፍና አገልግሎቱን የሚሰጡ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የጋግ ሩል ጫናን በመቋቋም አገልግሎቱን ለማስፋፋት ጥረት አድርገዋል። እ.ኤ.አ በ2018 እና በ2020 መካከል

- ጥንቃቄ የተሞላበት ፅንስ የማቋረጥ አቅም ያላቸዉ የመንግሥት የጤና ተቋማት ብዛት ከ67 በመቶ ወደ 83 በመቶ ከፍ ብሏል ።

- በጤና ተቋማት የሚሰጠው ጥንቃቄ የተሞላበት የፅንስ ማቋረጥ አገልግሎት በ10 በመቶ የጨመረ ሲሆን የድህረ ፅንስ ማቋረጥ አገልግሎት ደግሞ በ7 በመቶ ዝቅ ብሏል፡ ፡ ይህም የሚያሳየው የድህረ ፅንስ ማቋረጥ አገልግሎት የሚፈልጉ ሴቶች አነስተኛ መሆኑን ነው።

## ምክረ ሀሳብ

ባለፉት አስርተ አመታት የኢትዮጵያ መንግስት የሴቶችን የተዋልዶ ጤና ፍላጎት በማሟላት ረገድ ከፍተኛ መሻሻልን አሳይቷል። ሆኖም ግን የአሁኑ ግሎባል ጋግ ሩል ይሰጡ የነበሩ የተዋልዶ ጤና አገልግሎቶችን ከሟቋረጡም በላይ የተገኘውንም ውጤት ወደ ኋላ መልሶታል። የኢትዮጵያ ሴቶች የተዋልዶ ጤና መብትና የፅንስ ማቋረጥ አገልግሎትን የማግኘት ሁኔታ በሌላ አገር ውስጥ በሚደረግ የፖለቲካ አስተዳደር ለውጥ ሊወሰን አይገባውም። የጋግ ሩልን የአሜሪካ መንግስት እንደገና የሚተገብረው ከሆነ ኢትዮጵያ የህዝቧን የተዋልዶ ጤና ፍላጎት ከማሟላትና አገልግሎቱን ከማስፋፋት ረገድ ያላትን ነፃነት ለማስጠበቅ ወሳኝ ተግባራት ማከናወን ይገባታል። እነዚህም፡-

- የመንግስት የሲቪል ማህበረሰቡንና የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ትብብር በማጠናከር ረገድ ንቁ የሆነ የተግባር እንቅስቃሴ ያስፈልጋል፡ ፡ ይህም የተዋልዶ ጤና አገልግሎቶችን ሳይቋረጡ እንዲሰጡ ከማድረጉም በላይ የሴቶችን የተዋልዶ ጤና መብት ለማስከበር ያስችላል።

- አሜሪካ ውስጥ ያሉ የመብት ተከራካሪዎች (advocates) የግሎባል ጋግ ሩልን በቋሚነት ለማስቀረት በኮንግረሱ ላይ ግፊትና ጫና ማድረግ ይገባቸዋል። ይህም ፖሊሲው በኢትዮጵያና በሌሎችም ክፍለ አለማት የሚገኙ ሴቶች የተልዋዶ ጤና መብት መገፈፍ /መሸርሸር እንዳይቀጥል ያደርጋል።

- የጋግ ሩል እንደገና የሚተገበር ከሆነ ሁሉም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በፖሊሲው አተገባበር እና በሚያስከትለው ጉዳት ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ መንግስት፣ የሲቪል ማህበረሰቡና አለማቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በጋራ መስራት ይገባቸዋል።

- ከአሜሪካ የገንዘብ ድጋፍ ጥገኝነት ለመላቀቅና ወደፊትም ፖሊሲው ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳትና ተፅዕኖ ለመቋቋም የኢትዮጵያ መንግስት የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልገውን የገንዘብ ድጋፍ ማግኛ ምንጬን ማስፋት ያስፈልገዋል።

**ምንጭ**

ይህ ፅሁፍ “የትራምፕ አስተዳደር ያጠናከረው የግሎባል ጋግሩል በኢትዮጵያ የቤተሰብ እቅድ ፕሮግራም ላይ ያስከተለው ተፅዕኖ” በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ በ2022 በሱሊ፣ ሰለሞን አሰፋ፣ አሰፋ ስሜ፣ ቤል እና ጎርጊዮ ከተዘጋጀ ያልታተመ ጥናት የተወሰደ ነው። ተጨማሪ መረጃ ከዚህ ድረ ገፃ ማግኘት ይቻላል። https: //doi.org/10.1111/sitp.12196

**ምስጋና**

ይህ ጥናት ከዴቪዲና ሉስሊ ፓካርድ ፋውንዴሽን፣ ከአኒነመስ ፋውንዴሽን እንዲሁም በዊሊያምና ፍሎራ ሄውለት ፋውንዴሽን በተገኘ የግንዘብ ድጋፍ የተከናወነ ነው። በዚህ ጥናት ውስጥ የተገለፁት ጉዳዮች የአጥኚዎቹን ሀሳብ እንጂ በገንዘብ ድጋፍ ያደረጉ ድርጅቶችን አቋምና ፖሊሲ የሚያንፀባርቁ አይደሉም። ይህ ጥናት ሲጀመር ትብብር ላደረገው በጆን ሆፕኪንስ ብሉምበርግ የፐብሊክ ስኩል ውስጥ የሚገኘው ፐርፎርማንስ ሞኒተሪንግ ፎር አክሽን ምስጋና ይገባዋል።

www.ipas.org/where-we-work/ethiopia

www.aau.edu.et

Performance Monitoring and Accountability 2020

www.pmadata.org

Find this fact sheet online, in English, Amharic and Afan Oromo, at https://www.guttmacher.org/fact-sheet/impact-trump-administrations-global-gag-rule-sexual-and-reproductive-health-ethiopia. Additional information on sexual and reproductive health in Ethiopia is available at https://www.guttmacher.org/regions/africa/ethiopia.

**Good reproductive health policy starts with credible research**

**guttmacher.org**

125 Maiden Lane
New York, NY 10038
212.248.1111
info@guttmacher.org

NOVEMBER 2022